አንዳንድ ሰዎች፣ ካንሰር ያለባቸው መሆኑን ሲያውቁ፣ የሚሞቱ ይመስላቸዋል:: ነገር ግን ይህ ሁል ጊዜ ዕውነት አይደለም:: ብዙ ሰዎች፣ የካንሰር ህክምና ከተደረገላቸው በኋላ፣ ለረዢም ጊዚያት ጤናማ ሆነው ይኖራሉ:: የሳይንስ ጠቢባንም (ሳይንቲስቶች)፣ በሚመጡት ዓመታት፣ ከካንሰር የሚተርፉ ሰዎች ቁጥር እንደሚጨምር ይጠብቃሉ:: የማጣራት ምርመራዎች (ማለትም፣ የበሽታው ምልክቶች ከመታየታቸው ቀደም ብሎ የካንሰሩን መኖር አለመኖር ለማየት የሚደረግ ምርመራ) እደገትና መሻሻል፣ ቀድሞ ማግኘት (ማለትም፣ የካንሰሩ መጠን ገና ትንሽ ባለበትና ምንም ዓይነት ችግር ሊያስከትል በማይችልበት ደረጃ ላይ ሳለ መርምሮ ማግኘት)፣ እና የካንሰር ህክምናውን ማድረግ ናቸው ብዙ ሰዎችን ካንሰሩ ከተገኘባቸው ብኋላ ላሉት በርካታ ዓመታት እንዲኖሩ የሚያደርጓቸው:: ካንሰርን ተቋቁሞ ለመኖር የሚያስችለው አንዱ ቁም ነገር፣ ካንሰሩን ቀድሞ የማግኘቱ ጉዳይ ነው:: የበሽታው ቀድሞ መገኘት ማለት፣ ረዢም ዕድሜን ለመኖር ያለው ዕድል ከፍ ያለ ነው ማለት ነው:: ስለዚህ÷ የማጣራት ምርመራን በሚመለከት ዶክተርዎን ያማክሩ፣ እንዲሁም ስለተለያዩ የካንሰር ዓይነቶች የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ይጠይቁ:: ያስታውሱ÷ ከካንሰር መትረፍ ይቻላል!

Some people believe that having cancer means they will die, but that is not always true. Many people live long, healthy lives after they have cancer treatment. And scientists expect the number of cancer survivors to increase over the coming years. Improvements in screening tests (examinations that look for cancer early before symptoms), early detection (finding the cancer early when it is smaller and not causing any problems), and cancer treatment are things that allow more people to live following cancer each year. One very important part of surviving cancer is finding it early. The earlier the disease is diagnosed, the better chances are for living a long life following a cancer. So, talk with your doctor about screening tests, and ask about the warning signs of different types of cancer. Remember, it is possible to survive cancer!